# ሥልጡኑ ጎረቤቴ እና እኔ
## ክፍል ሁለት

በልጅግ አሊ

-፩-

ጎረቤቴ አንድ ቀን ወደ ቤቴ ብቅ ብሎ ከወትሮ በተለየ ረጋ ባለ ሁኔታ ትዳር መያዝ እንደፈለገ ነገረኝ ። እኔም የትዳርን ጥሩነትና አሁን ወቅቱ እነደሆነ አስረድቼው ጨዋታችንን ቀጠልን ።

"ለመሆኑ ጓደኛ አግኝተሃል እንዴ?" ብዬ ጠየቅሁት ግንኙነቱን እንዳልሰማሁ ሁኜ ።
"አልሰማህምና ነው የምትጠይቀኝ ?"አለኝ ሁሉም ሰው እንደሚያወራውና እኔም መስማቴን እርግጠኛ በመሆን ።
"ዘንድሮ ምን የማይተማ ነገር አለ ብለህ? ካንተው አፍ ልስማ ብዬ ነው እንጂ " አልኩት ።
"ታውቃት የለም ሩት የምትባለው ልጅ እኮ ነች ። ለነገሩ እውነተኛ ስሟ መቅደስ ነበር ። እዚህ ስሟን ቀይራ ነው ።"
"እንዴ እሷ ኤርትራዊ ነች ይሏት የለም እንዴ ?" ብዬ ጠየቅሁት ምን ያህል መለወጡን ለመረዳት ።
"ማነው ያለው ? መቼም የማይሉት የለም አለኝ " ከዚህ በፊት እራሱ እነደነገረኝ በመርሳት ። ግን ያንን ማንሳትና መከራከር ለዛሬው ውይይት አስፈላጊ ስላልሆና እሱም ራሱን አወዛውዞ "ሰው ከሰው ራስ ላይ አይወርድም ብላለች ቀበሮ"ብሎ ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ተረት ሲፈጥር ሳየው ሌላ ነገር ሳይቀጥል ብዬ ፡ -
"ታዲያስ ምን ልታደርግ ነው ያሰብከው?" ብዬ ጠየቅሁት።
"አጠር ያለች ሠርግ ቢጤ ለመደገስ አሳብ አለኝ ።የመዘጋጃ ቤቱ ፊርማ ግን ይቆያል ። ለማንኛውም ፊርማው ምን ያስቸኩላል ፣ እስቲ ባይሆን ቀብድ ትያዝና ፊርማውን እናስብበታለን አለኝ" ።
"ቀብዱ ደግሞ ምንድነው አልኩት ?"
"ትንሽ ሆዷ ይበጣ ! " ብሎ ባሽሙር ታርግዝ ማለቱን መሆኑን ነገረኝ።
"ገና ለገና አንተ ፈርመህላት የዚህ ሃገር ወረቀት እንድታገኝ ተብሎ ልጅ መውለድ አለባት ? ይህ ምን ዓይነት ሰብአዊነት ነው ? የሚወለደውስ ልጅ እንደልጅህ ትቆጥረዋለህ ? " አልኩት።
"ይህንን ኋላ የቀረ የኮሚኒስቶች አስተሳሰብህን ተወው ። ለኛም አልጠቀመን ። በኋላ ፈንግላኝ ጥላኝ ከሄደች በኋላ ጨርቄን ጥዬ በየከተማው ስደነፋ ብውል፣አበድኩ ብል! ማን ይደርስልኛል ? በዛ ላይ ደግሞ እኔ አይደለሁም ይህንን ያመጣሁት ሥርዓቱ ነው ከፈለግህ እሱን ተዋጋ ። ስማኝ ደግሞ የዘንድሮ ልጆች እዚህ አውሮፓ እስከሚደርሱ ስንቱን እንዳዩ አታውቅም እንዴ ? እኔ እኮ አግብቻት ፣ ትዳር ይዛ ፣ ወረቀቷ ተስተካክሎ ፣ ቤተሰቧን እየረዳች እንድትኖር ነው ጥረቴ። አይ አንተን አልፈልግም ካለች ደግሞ ጥቅሜንም መተው ነውውው . . . . . ። ከአውሮፓ አውሮፓ ስትልከሰከስ ትኖራታለች እንጂ የመላ አማራንም የድጋፍ ወረቀትም ሆነ የዚህ ሃገርንም መኖሪያ አታገኛትም ። ለማንኛውም ለጫወታው አነሳሁት እንጂ የእኛ በሁላችንም መፈቃቀድ ነው ጋብቻው። ብትፈልግ ልትጠይቃት ትችላለህ " አለኝ። እኔም ከዚህ በላይ ሄጄ በጽሞና የያዘችውን የልጅቷን ጉዳይ አላበላሽም ብዬ ነገሩን ለማለዘብ ያህል ፡ -
"ታዲያ እንዴት ነው የምረዳህ? አልኩና ጠየኩት ።
"አነስተኛ አዳራሽ ይዘናል ። ሠርጉም በበጋ እንዲሆን ተወስኗል ። የምናደርገው አነስተኛ ሠርግ ነው።ከሃምሳ እስከ መቶ ሰው ብንጋብዝ ነው ። አንተም እንድታስተናግድልኝና እኔን ሆነህ የጎደለውን ሁሉ እንድታይልኝ እፈልጋለሁ " ። አለኝ እሺም እምቢም ሳልል በሃሳብ ተውጬ ዝም አልኩ።

ጎረቤቴ እና እኔ የተተዋወቅነው ወያኔ ሥልጣን ላይ ወጥቶ የአማራ ዘር በሙሉ ይጨፍጨፍ ተብሎ በሚሰበክበት ፣ ኤርትራውያን ከትግራይ ልጆች ጋር በማበር በፀረ አማራ አቋም ያበሩበት፣ ወያኔዎች ኢትዮጵያ የሚባል ሃገር መስማት የማይፈልጉበት፣ አድርባዮች ወያኔ በፈለፈላቸው የዘር ድርጅቶች በሚሰገሰጉበት ፣ ምሁራን ነን ባዮች ከመላው ዓለም ሥልጣን ይገኛል ብለው ወደ አዲስ አበባ ያመሩበት ፣ስደት በሰፊው የተጀመረበት እና በዘር መደራጀት ፋሽን የሆነበት ወቅት ነበር ።

በወቅቱ ሁሉም ሰው ሲገናኝ ስለ ፖለቲካ ማውራትና መወያየት የተለመደ ነበርና ከጎረቤቴም ጋር በተገናኘን ቁጥር ምን አዲስ ዜና አለ? ብለን መጠያየቅ ጀመርን። ከዛም ችግርን መካፈል ፣ ስለስደተኝነት ጥያቄያችን ማውጋት የበለጠ አቀራረበን።በተለይ በምንኖርበት አካባቢ የነበሩት ቀደም ብለው የመጡ የትግራይና የኤርትራ ልጆች ከሚያወቋቸው ፈረንጆች ጋር በማበር መቆሚያ መቀመጫ ስላሳጡን ፣ በየፈረንጆቹ ቢሮ እየሄዱ ጥገኝነት ስለሚጠይቀው ስደተኛ የደርግ ደጋፊ ነበሩ እያሉ በመናገር የስደተኛ ጥያቄያችን ተቀባይነት እንዳያገኝ እየሞከሩ ስለነበር መተባበር ግዴታ ነበርና ተባብረን እንታገላቸው ጀመር።

ያለንበት ሃገር መንግሥት ይቀበለዋል ብለን ያሰብነው የስደተኝነት ጥያቄችን አዘጋጅተን፣ በተለይ ትምህርታችንና ዕድሜያችን እንዳይቃረን ሁለት ክፍል እየዘለልን እያስተካከልን ፣ ከትምህርታችን ደግሞ እድሜ ሲበልጥ በፖለቲካ እስረኝነት እንዳሳለፍነው እያሳበብን የሕይወት ታሪካቸችንን አዲስ ፅፈን አዲስ ኑሮ ጀመርን። ለሁላችንም ይስማማናል ወይም አንረሳውም ያልነውን ታሪክ ጽፈን አዘጋጀን ። ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ቀደም ብለው የመጡ ኢትዮጵያውያን በዚህ በኩል በአያሌው ረድተውናል ። ጎረቤቴ አዲስ የተፃፈለትን እንደ እውነት ወስዶ፣እኛው የፈጠርንለት የጥገኝነት ታሪኩ መሆኑን አንዳንዴም እየዘነጋ፣ አልፎ ተርፎ ያልነበረበትንና የማያውቀውን ለኛው ለራሳችን በሰፊው ማውራት ተያያዘው። ይሁንለት ፣ ይመቸው ብለን እኛም ዝም አልን ።

ወያኔ ሥልጣን በያዘበት ጊዜ በደርግ ደጋፊነት መታማት አስከፊና የተዋረደ ስለነበር ( አሁንም በሕዝብ መሃል የተዋረደ ነው) በወሬ ወሬ የሰሙትን ሰብስበው "ኢሕአፓ አባል ነበርን" ባዩ በዝቶ ነበር። ጎረቤቴም ምንም እንኳ ከምስራቅ አውሮፓ የመጣ ቢሆንም ምን ለመማር እንደመጣ ሳይናገር የድሮ "የኢሕአፓ አባል ነኝ" ብሎ ከደርግ ሥርዓት ራሱን አራቀ።

በዚያ ወቅት ወደ ምዕራብ አውሮፓ የፈለሱት ኢትዮጵያውያን በምሥራቅ አውሮፓ ትምህርት ላይ የነበሩ ወይም በኤምባሲዎች ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ናቸው ።በምሥራቅ አውሮፓ ይማር የነበረው ተማሪ ሦስት ዓይነት ነው ። አንደኛው ክፍል የአካዳሚ ትምህርት ለመማር የመጣ ሁለተኛው ደግሞ የፖለቲካ ተማሪ ሦስተኛው ደግሞ የሠራዊቱ አባላት የነበሩ ናቸው ። የፖለቲካ ተማሪዎቹ ብዙዎቹ በኢሠፓ አባላትነታቸው ምክንያት እንደ ሽልማት የውጭ ትምህርት ዕድል የተሠጣቸው ሲሆኑ በሠራዊቱ ውስጥ ታማኝ ሆነው የቆዩ ደግሞ ስለጦር ትምህርት እንዲማሩ የተላኩ ነበሩ። በአካዳሚው ክፍል ደግሞ በሁለት ይከፈላል ። አንደኛው ክፍል የትምህርት ነጥቡ ከፍተኛ ሆኖ ለትምህርት በቂ ዕውቀት ያለው ሲሆን ( ይህ ደግሞ ፀረ አብዮት ውስጥ ያልተሳተፈ መሆን ይኖርበታል ። ይህ ግን እየቆየ የተረሳ ነበር ።) ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በትምህርቱ ሳይሆን በሕዝባዊ ድርጅቶች ( አኢሰማ ፣ አኢወማ ፣ አኢገማ ፣ መኢሰማ ፣ . . . ) ውስጥ በመሳተፍና ፀረ አብዮተኞችን በመዋጋት የተባበሩ፣ባቀረቡት የድጋፍ ወረቀት ምክንያት ለውጭ ትምህርት ዕድል የተመረጡ፣ ጠንከር ያለ ዘመድ ያለቸው ነበሩ ። ዘመድ ደግሞ በሃገርና በሥልጣን ይከፈላል ። በደርግ ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣን ዘመድ ያላቸው ወደ ምሥራቅ ጀርመን ሲላኩ የሌላቸው ደግሞ ወደ ቀድሞው ሶቪየት ሕብረት ነበር የሚላኩት።ዛሬ ምዕራብ አውሮፓን ያጥለቀለቀው ኢትዮጵያዊ እንደዚህ ዓይነት ስብጥር ያለው ነው ።

ጎረቤቴ ከላይ በጠቀስኳቸው ውስጥ ራሱን ባይመድብም የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ፈተና (ማትሪክ) ከፍተኛ ውጤት እንደለው ይናገራል ። ዕውቀቱን ለገመገመው፣ ሁኔታውን ላጤነው ግን የድጋፍ ወረቀት ከየቀበሌው አፅፈው ባለሥልጣን ዘመድ አፈላልገው ከመጡት ተማሪዎች ውስጥ ይመድበዋል ። አንዳንዴም በቅርብ ከሚያውቁት ሰዎች የምንሰማው ሃሜት ይህንን የሚደግፍ ይመሰስላል።ስለትምህርት ወይም ዕውቀት ብዙም የማይጨነቅ ሲሆን ብዙውን ግዜውን ከሰዎች የሰማውን እንደ በቀቀን ወፍ በመድገም አዋቂ መባልን ይመርጣል ። ጎረቤቴ ቤት ውስጥ ያለው መጽሐፍ የስልክ ማውጫና ፣ የባንክ ደብተር ብቻ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም ።ባለፈው እንደተጨዋወትነው "ኢየሱስን ተቀበልኩ" እያለ ሰው ያስቸገረበትን መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ "ከቸርች" የተዋሰው ነበር። እሱንም ቢሆን ለይስሙላ በእጁ ይዞ አንገላታው እንጂ እንዳለነበበው ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ ።

ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች እንደ አሸን ሲፈሉ ጎረቤቴ የድሮ ኢሕአፓ አባልነቱን ቀስ አድርጎ በመተው በቅርብ የተቋቋመው የመድህን ደጋፊ ሆነ ። የመድህን "ደጋፊ ሆነ" ሆነ ብዬ ማለፍም ይከብደኛል።ጎሹ ወልዴን ያመልክ ጀመር ብል ማጋነን አይሆንም። በመድህን ድርጅት ውስጥ የተሰበሰበው የኢሠፓ አባል ለጎረቤቴ የመታወቅ አባዜ ቦታና ዕድል ስላልሰጡት በገባበት ፍጥነት እራሱን ከመድህን አገለለ ።በዚህ ተገርመን ሳናበቃ የመላው አማራ ድርጅት ሲመሠረትና ኃይሉ ሻውል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አውሮፓ ብቅ ሲሉ በቀዳሚነት የመላው አማራ አባል ሆነ።ጎረቤቴም መላው አማራን ከልቡ የሚደግፍ ይምሰል እንጂ ለወረት ብሎ የተጠጋ መሆኑን ለኔ ግልጽ ነበር ። በወቅቱ በአማራ ላይ በተፈፀመው አስቃቂ ግድያ ምክንያት ያለንበት ሃገር ለመላው አማራ ድርጅት አባላት ነን ለሚሉ የፈቃድ ወረቀት ስለሚሠጡ አዲስ ስደተኞች ወደዚህ ድርጅት መጉረፍ ጀምረው ነበር።

ታዲያ ጎረቤቴ ምኞቱ ተሳክቶለት የድርጅቱ ተመራጭ ሆኖ በሚጣደፍበት ወቅት ነው አንዲት አካባቢያችን የምትኖር የመኖሪያ ፈቃድ ያለነበራትና በጣም የተቸገረች ወጣት ሴት የተዋወቀው። በመጀመሪያ ኤርትራዊ መሆኑዋን ሲሰማ ያበሻቅጣት ጀመር። እረ ተው አንዲት ምስኪን ሴት ብንለውም እንቢ አለ። ልጅቷ እንዴት እንደተግባባችው ሳናውቅ በአንድ ጊዜ ስለ ልጅቷ ጥሩነት ማውራት፣ አልፎም መርዳት ጀመረ ። አማራነታቸው ሳይጣራ የድጋፍ ወረቀት ለማንም አይሰጥም እያለ ቡራ ከረዩ ይል የነበረው ፣ በዚህች ልጅ ሁኔታ ልቡ መጨከን አቃተው ። አብሮ የተወለደ ይመስል አንዳንዴም የልጅቷን አማራነት መስካሪ ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ መላው አማራ የሁሉም ዘር ድርጅት ነው በማለት በድርጅቱ ውስጥ ስለ ዘር መነሳትን መቃወም ቀጠለ።

ልጅቷ ምንም እንኳ ከቤተሰቦችዋ አንዱ ክፍል የኤርትራዊነት ሃረግ ይኑራት እንጂ ትግርኛ እንኳ የማታውቅ አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገች ነበረች ። ኤርትራውያን **አሚቼ**( ኤርትራውያን አዲስ አባበ ላደጉት ኤርትራውያን ያወጡት ቅጽል ስም

ነው። ትርጉሙም አዲስ አበባ ውስጥ የነበረውን የመኪና መገጣጠሚያ ይመለከታል። ለማለት የፈለጉት የተገጣጠመ ኤርትራዊ ነው)ብለው ሲያባርሯት እንደ ጎረቤቴ ያሉት ደግሞ ሻዓቢያ እያሉ መቆምያ መቀመጫ ያሳጥዋት ሰው ነበረች።

በዚህ ቀውጢ ጊዜ ጉዳይዋ ኢትዮጵያዊ ነኝ አትል በዘር ሃረጓ ውስጥ ኤርትራ አለ ፣ ኤርትራዊ እንዳትሆን እነ ኢሳያስ በስደተኛው ላይ የጣሉትን መዋጮም ይሁን ኤርትራ ትገንጠል የሚለውን ሬፈረንዶም አላደረገችም ። የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ነውና ጎረቤቴን የመጠጋቱ ሁኔታ ሌላ አማራጭ የሌለው ነበር ።ጎረቤቴም እሷን ከተገናኘ ጀምሮ እንዲያ ሲጠላው የነበረውን የትግሬ ዘር አሁን በሙሉ ልቡ ለመሳደብ አፉ ተያዘ ። እንዲያውም አመለካከቱ በአስቸኳይ ተለውጦ ዓለም አቀፋዊነት ላይ ያተኮረ ስለሆነ አብረውት ተሰብስበው የነበሩትን ማስደንገጥ ጀምሮ ነበር ።

ሠርጉ በተወሰነው ቀን አነስተኛ ሳይሆን በሊሞዚንና በተከራዩት ማርቼዲስ ታጅበው ደረሱ ። ብዙው ተጋባዥ ይህንን ጉድ ሲመለከት "ምነው ሎተሪ ደረሰው እንዴ? " እያለ ማሽሟጠጥ የጀመረው ወዲያው ነው ። ሙሽሮቹ በዘፋኝ ታጅበው ግራና ቀኝ ችቦ እየተበራ ፣እልል እየተባለ ተደገሰ ። ችግሩ ግን እሱ እንዲያ ሲንጎማለል ልጅቷ ግን መንቀሳቀስ ያቃታት ወሯ የገባ ቅሪት ነበረች። መቼም የሃገር ወግ ነውና እስክስታ እንድትል የሰከረ ሁሉ ሠርገኛ ሲጋብዛት ፣ የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዱ ሲባል ፣የሷ ዘመዶች እንዳይሸነፉ ተንደርድራ ስትገባ ፣ ከአሁን አሁን ችግር ገጠመን ብለን ሰውነታችን ሲያልቅ ድግሡ በሰላም አለቀ።

ሠርጉም አልቆ ልጅ ተወልደ። "ለክርስትና ! አሆሆ ! ለክርስትና እንመጣለን ገና !!!!" . . . እንዳልነውና ቀጠሮ እንደያዝነው ክርስትና ተጋበዝን ። ጎረቤቴ ቤት ድግስ አያልቅምና ስለድግስ እዚሁ ላይ ላቁም ።ከድግሡ ማግሥት "በመላ አማራ ድርጅት ገንዘብ ሠርግ ደገሱበት ፣ ጨፈሩበት" የሚለው ወሬ መወራት ጀመረ። እኔ ደግሞ ውስጠ ምሥጢር አዋቂ ስለሆንኩ ገንዘቡ የባንክ ብድር እንጂ የሕዝብ እንዳልሆነ ለወሬው ምንም ቦታ ሳልሰጠው አለፍኩት። ይህ መሠረተ ቢስ አሉባልታ በድርጅቱ ውስጥ ለተነሳው የውስጥ ክፍፍልና ለስም ማጥፊያ ተጠቀሙበት እንጂ ጎረቤቴ የሆዱን በሆዱ ችሎ ብድሩን መክፍል ከጀመረ ሰንብቷል።

የመላው አማራ አባላት በጎጥ ተከፋፍለው ሲናወጡ ጎረቤቴ ትልቅ ይላቸው የነበሩትን መሪዎች በመሳደብ ድርጅቱ እንዲፈርስ ያጣጥል ጀመር ። እንዲውም ይባስ ብሎ እንደዛ ሲታገልለት የነበረውን ድርጅት በየስብሰባው በግልጥ መስደብ ተያያዘው። መሪዎቹን ማዋረዱን በሰፊው ቀጠለ። በዚህ በተነሳው ጠብ ድርጅቱም በአካባቢያችን እየደከመ መጣ ። ሚስቱም የምንኖርበት ሃገር መንግሥት ካለእሱ እርዳታ በሰብዓዊነት ወረቀት ሰጣት ። ጎረቤቴም የሚስቱም ጉዳይ ሲፈፀም ፣ የባንኩ እዳም ለመክፈል ብዙ መስራትን ሲጠይቅ ፣ ልጅ የማሳደግና የቤተሰብ ሃላፊ መሆን እየተጫነው ሲመጣና በድርጅቱ ውስጥ ያለው ችግርም እየባሰ ሲመጣ ድርጅቱን ትቶ አርፎ ተቀመጠ።

ጎረቤቴ እንደገና ወደ ፖለቲካው ዓለም የተመለሰው በሚያስገርም ሁኔታ ነው ። የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት ላይ ሃገራችን ተወረረች ብሎ ዋና አስተባባሪ ሆነ ። ወያኔ በጠራው ስብሰባ ላይ በመገኘት ንግግር ማድረግ ጀመረ ። "ባድሜ ላይ ሕይወታችንን እንሰጣለን "ድንበራችን ቀይ ባሕር ነው" እንዳላለ አሁን ደግሞ "ዛላአንበሳ የኛ ነው" የሚለውን መፈክር አንግቦ ተነሳ። ግን በዚህ ወቅት ብዙዎች የወያኔ ደጋፊዎች ያጨብጭቡለት እንጂ ቦታ ሊሰጡት አልቻሉም ። በአካባቢው ከእሱ የተሻሉ አድርባዮች ነበሩና ።

ከዚህ ሁሉ የፖለቲካ ጅምናስቲክ በኋላ ነበር ጎረቤቴ ሃይማኖቱን የቀየረው ።

ሲመች ይቀጥላል ።

ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም !

በልጅግ አሊ

Beljig.ali@gmail.com